ወላሂ አላመነም! ወላሂ አላመነም! ወላሂ አላመነም!" "የአላህ መልክተኛ ሆይ ማን ነው?" ተባሉ። እርሳቸውም "ጎረቤቱ ተንኮሉን ያላመነው ሰው ነው።" አሉ።

ከአቡ ሹረይሕ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ አሉ፦ «"ወላሂ አላመነም! ወላሂ አላመነም! ወላሂ አላመነም!" "የአላህ መልክተኛ ሆይ ማን ነው?" ተባሉ። እርሳቸውም "ጎረቤቱ ተንኮሉን ያላመነው ሰው ነው።" አሉ።» [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ማሉ። መሃላቸውንም ሶስት ጊዜ አድርገው አፅንዖት ሰጥተው እንዲህ አሉ: "ወላሂ አላመነም! ወላሂ አላመነም! ወላሂ አላመነም!" አሉ። ሶሐቦችም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ማን ነው ያላመነው?" አሉ። እርሳቸውም "ከክዳቱ፣ ከግፉና ከክፋቱ አንፃር ጎረቤቱ የሚፈራው ነው።" አሉ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/66268